# ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው
# የተዋሕዶ አንበሣም መድኃኒዓለም
# ኢየሱስ ክርስቶስ ነው



ከአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ



ቅድስት እምቅዱሳን ንጽሕት እምንፁሐን እመአምላክ ድንግል ማርያም
የኢትዮጵያ እናት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
ዘኢትዮጵያ



የመጽሐፉ ደራሲ
አባ ተስፋ ስላሴ ሞገስ

መጽሐፉን ያለ ደራሲው ፈቃድ ማሳተምም ሆነ መተርጎም በሕግ ያስጠይቃል ።

ALL RIGHTS RESERVED



ሰማዕቱ ቅዱስ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ የነበሩ

## መ ታ ሰ ቢ ያ ፤

ይህ ምርምራዊ የሆነ የእምነት መጽሐፍ በሰማዕቱ አባቴ በብፁዕ ወቅዱስ የእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትር ያርክ በነበሩ በአቡነ ቴዎፍሎስ ስም ሰይሜዋለሁ ።

# ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው
# የተዋሕዶ አንበሳም መድኃኔ ዓለም
# ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

## ማውጫ

## ፩· ማስገንዘቢያዎች


ገጽ

ሀ· የተዋሕዶ አንበሣ ፤ የከሃዲዎች መዶሻ ............ 19
ለ· ማሳሰቢያ ለአንባብያን ............ 20
ሐ· የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ............ 21
መ· ምስጋና ............ 22

ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት ............ 23
መግቢያ ............ 24
መቅድም ............ 26


## ክፍል ፩

## ጥንትም ዛሬም የኢትዮጵያውያን አባቶች እምነት (ዶግማ) በዘመናዊ አገላለጽ ፤


ሀ· መለኮታዊ አምላክ ............ 28
1· ለፍጥረቱ ሁሉ ምንጭ የሆነ ፀሐይ ስም ............ 29

2· የእውነተኛው አምላክ የአንድነትና የሦስትነት ስም ............. 30
3· የአምላክ ስሞች ትርጉም በከፊል ............................................ 30
4· ሌላው ነቢይ ወይም መሲህ ................................................ 31


## ክፍል ፪

## የምሥጢረ ተዋሕዶ ትርጉም በምህጻረ ቃል (በአጭሩ)


ለ· የሚሞት ሥጋ የማይሞት መለኮትን ተወሐደ ......................... 32
1· ኃጢአት የማይስማማው የሰውን ሥጋ ተወሐደ ..................... 32
2· ረቂቅ መለኮታዊ ቃል በሥጋ ተገለጸ ........................................ 33
3· መለኮት የተወሐደው የሰው ልጅ ምራቅ የእውሩን ዓይን አበራ ........................................................ 33


## ክፍል ፫

## በማይታበል ቃሉ የመድኃኒታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ መልስ


ሐ· የእኔ አምላክነት በእርሱ ይገለጽ ዘንድ ነው .............................. 34
1· የዚህ ዓለም ብርሃን ማን ነው ........................................................ 35
2· ለዘለዓለም የማይጠፋ ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ............... 35
3· በአይሁድና በአምኖስ መካከል የነበረው ክርክር .................. 36
4· የፈሪሳውያን ጥያቄና የአምኖስ መልስ ........................... 38
5· በፈሪሳውያንና በአይሁድ መካከል መለያየት ተፈጠረ .......... 39
6· የአማን አምኖስና የፈሪሳውያን የሕቅታ መልስ ..................... 40




## ክፍል ፬

## አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት ፣ በባሕርይ በሕልውና አንድ አምላክ ናቸው ፣


1· ትክክል የሚሆኑ በመለኮት ፩ድም ፫ትም ናቸው ....................... 41
2· እኔ እውነተኛ መንገድ ነኝ ፣ በእኔና በአብ ፣ በመንፈስ ቅዱስ መካከል ልዩነት የለንም ፣ በስም ፫ት ስንሆን ፩ እግዚአብሔር ነን አላቸው 42
3· ሦስት ሲሆን አንድ አንድ ሲሆን ፫ት የሆነ ፈጣሪ (አምላክ) ........ 43
4· መለኮት በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሲሆን ሰውም በተዋሕዶ ፍጹም መለኮት ነው ........................................................................ 44
5· ጽዮን ታቦት ፣ ጽዮን ተራራ ፣ ጽዮን መጠጊያ ፣ ጽዮን ማደሪያ ፣ ጽዮን እናታችን ቅድስት ማርያም መማፀኛ .................................... 45


## ክፍል ፭

## የእምነት ልዩነቶች እንዴት ተፈጠሩ ?


1· ሰዎች ሥልጣን ፍለጋ በእምነት ሽፋን ስለሚነሱ ነው ............. 46


## ክፍል ፮

## ቀጥተኛዋና እውነተኛይቱ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ከ፪ት እንደተከፈለች ።


ሀ· የእምነት መሠረት ተዋሕዶ ነው ከ1–33–451 ዓ·ም· ............... 48

# ክፍል ፲፪

## በራሱ ጥበብ ዘለዓለማዊ የሆነ ኃይል በጣም አስደናቂ የሆኑ ሥራዎችን የሚ ሠራባቸው የጥበብ ስሞች ፤


ሀ·1· ራፋኤል ........................................ 78
ሀ·2· ኪሩቤልና ሱራፌል ........................................ 78
ሀ·3· ሣጥናኤል ........................................ 79
ሀ·4· በታማኝነት የቆሙ አለቆች ........................................ 80
ሀ·5· በ፬ቱ የሰውነት ክፍል የተሾሙ አለቆች ........................................ 80
ሀ·6· ፫ቱ ባሕርየ ነፍስ የአምላክ ናቸው ........................................ 81
ሀ·7· ፯ቱ ሊቃነ መላእክት የ፬ቱ መዓዝነ ዓለም ሹሞች ........................................ 81
ሀ·8· በዓይን ሲታዩ የሚያስደንቁ ኃይሎች ........................................ 82
ከሀ·፩ እስከ ሀ·፰ የተገለጹ ኃይሎች ........................................ 83


# ክፍል ፲፫

## በእናት ኢትዮጵያ በመሬት ውስጥ የተቀበሩ የፒራሚድና ሌሎች ከተሞች ማን እንደሰራቸው ፤


1· እንዴት ተሠሩ በማን እጅ ........................................ 84
2· በራሱ በራፋኤል እጅ የተሰሩ በ9630 ክ·ል· (B.C) ........................................ 85
3· በኪሩቤልና በሱራፌል እጅ የተሠሩ በ9600 ክ·ል· (B.C) ........................................ 85





4· በሣጥናኤል እጅ የተሠሩ በ8300 ክ·ል· (B.C) ........................................ 87
5· በዓይን ሲታዩ በሚያስደንቁ ኃይሎች እጅ የተሠሩ ፤
በ4300–3412–2780–2100–1510 ክ·ል· (B.C) ........................................ 89
6· በ፯ቱ ሊቃነ መላእክት የ፬ቱ መአዝነ ዓለም ሹሞች እጅ የተሠሩ ፤
በ3000–2000–1500–1000 ክ·ል· (B.C) ........................................ 91
7· በታማኝነት የቆሙ አለቆች እጅ የተሠሩ ፤
በ2900–1800–1400–900–600–300 ክ·ል· (B.C) ........................................ 92


# ክፍል ፲፬

## ትምህርተ መለኮት ምሥጢረ ሥላሴ በግብጽ ኮብቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አይታወቅም ፤


1· አካል የሌለው ስም በግብጽ ኮብቲክ ........................................ 94
2· አካል የሌለው ስም በዓለም ውስጥ አይገኝም ........................................ 95
3· በስም ፣ በግብር ፣ በአካል ፫ት በባሕርይ
በህልውና ፣ በመለኮት ፩ድ የሆነ አምላክ ........................................ 96
4· ጳጳሳት ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ለምን ይመጡ
እንደነበረና ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች ........................................ 99
5· በግዮን ወይም በአባይ ወንዝ ምክንያት
ከምሥር ጋር የተደረገው ጦርነት ........................................ 101


# ክፍል ፲፭

## ከዓለም ውስጥ አምኖ የተጠመቀ የመ ጀመሪያ ሰው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መልከ ጼዴቅ ፪ኛ/ ነው ፤


1· የተዋሕዶ አንበሳ ........................................ 105

# ለ· ማሳሰቢያ ለአንባብያን

በመጠኑም ቢሆን በመቅድሙ ላይ የገለጽኩት ቢሆንም ክፍል ፲፪ እና ፲፫ በዚህ ጥናት ውስጥ የገባው ምንም እንኳን የእምነት ይዘት ቢኖረውም በእምነትነቱ ሳይሆን ነገር ግን በአስደናቂ ታሪክነቱ ብቻ ነው ።

ይህም ኢትዮጵያውያን አባቶች የደረሱበትን በጣም ረቂቅ የሆነ ጥበብና ምሥጢር ሌላው ዓለም እስከ ዛሬ ድረስ ያልደረሰበትና ለወደፊቱም ቢሆን ሊደርስበት የማይችል ጥበብ መሆኑን ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ስገልጽ በትህትና ነው ።

እንዲሁም ደግሞ በተጨማሪ ክፍል ፩·፲፪·፲፫ በአሜሪካን ውስጥ በሁለት የምርምርና የጥናት ማዕከል በእነዚህ በተጠቀሱት ቁጥሮች ርዕስ አጥንቼ እንዳቀርብ በተጠየኩት መሠረት የተዘጋጁ ናቸው ። ስለዚህ ኢትዮ፡ያውያን ወገኖቼ በቅድሚያ ማወቅ ስላለባቸው በዚህ ታሪካዊ የሆነ ጥናት ውስጥ እንዲገቡ ማድረጌን በታላቅ አክብሮት እገልጻለሁ ።

ይሁን እንጂ ሰዎች ስለ ሃይማኖትና ስለ ሌላም በጣም አስደናቂ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ማለትም ለመጠየቅና ለማወቅ አእምሯቸው ውስጥ የሚመላለሱትን ሁሉ አብዛኞቹ በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱ ስለሆነ ፤ እስከ መጨረሻው ድረስ በትዕግሥትና በጽሞና አንብበው ከእኔ የተሻለ የእርምት ፍሬ ሐሳብ እንዲሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ ፡…



# ሐ· የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ

ይህ ጥናት ስለ ኢትዮጵያ ቀጥተኛዋ ተዋሕዶ እምነት ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ያለውን ልዩነት በማነጻጸር ግልጥልጥ አድርጐ ፊቱን መስታወት እንደሚያይ ሰው የሚያስረዳ ነው ብዬ አምናለሁ ።

እስከዛሬ ድረስ የዚህ ዓይነቱ ጥናት ቀርቦ አያውቅምና ነው ። ይህንንም ያልኩበት ምክንያት በእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ሊቃውንት እጅ የተጻፉ መጻሕፍት ከመላ ጉዶል በእኔ እጅ እንኳን የሚገኙ መጻሕፍት እስከ ዛሬ ድረስ ፭፻፲ ሲሆኑ አብዛኞቹ ተመሳሳዮች በመሆናቸው በማስረጃነት ወይም በዋቢነት የጠቀስኳቸው ፪፲፰ መጻሕፍት ብቻ ናቸው ።

ከእንግዲህ ወዲህ አባቶቼ የእናት ኢትዮጵያ ሊቃውንት የተሻለ መጽሐፍ እንዲጽፉ በማሳሰብ የእኔንም ጥናት ስህተት የመሰላቸውን ቃልና ፀረፍተ ነገር እንደሚያርሙኝ በማመን በትህትና አቅርቤያለሁ ።

ወልዱ ለሣሙኤል ዘገዳመ ዋሊ ዋልድባ አብረንተአንት ፣ ዋሊ ከቡልጋ ሄደው የተሰወሩ 12,000 ሰዎችና የቅዱሳን ምግብ የሆነች እንደ ግርና ወተት የምትጣፍጥ ዕጽ ናት ።

የተከበራችሁ አንባብያን <u>አርቶዶክስ</u> የሚለው ቃል ግሪክኛ እንጂ ኢትዮጵያዊኛ ስላልሆነ ከላይ የኢትዮጵያ <u>ቀጥተኛ</u> ተዋሕዶ ብየዋለሁ ፤ በዚህ ጥናት ውስጥም ከእነልዩነታቸውና አመሠራረታቸው ሳይቀር እንደ አመጣጣቸው በቅደም ተከተል በሚገባ የተብራራ ስለሆነ ያለምንም ችግር በቀላሉ መረዳት ይቻላል ፡…

1984 – 1988 ዓ·ም·

# መ. ምሥጋና

## በማንኛውም ጉዳይ ሁሉ ለተባበሩኝ እና ለሚረዱኝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ

፩ኛ) እንደ አይሁዶች ስድባቸውን ሁሉ አስወግዶ የእናት ኢትዮጵያ ምርጥ ሕዝብ ላደረጋቸው ለጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሙሉ ፣ በኢትዮጵያ ውያን አምላክ በሕያው እግዚአብሔርና በንጽሕት ቅድስት እ፣ቱ በድንግል ማርያም ስም ሳመሰግናቸው በጣም ከፍተኛ የሆነ ፤ልብ ደስታ እየተሰማኝ ነው ።

፪ኛ) በኮምፒዩተር ለመጻፍ ለተባበረችኝ ለወ/ሪት አስናቀች እንዳ፣ካቸው ቅዱስ ሚካኤል እንዲጠብቃት ከልብ እመኝላታለሁ ፤ ፦ጥሎም ምንም እንኳን የምጽፈው የእምነት መጽሐፍ ቢሆንም ገየቀኑ የጻፍኩትን በመናበብና ሐሳብ በመስጠት ለረዳኝ ለአቶ ታመነ ግዛው ቅዱስ ገብርኤል ይጠብቀው ። እንዲሁም በኮምፒዩተር የተጻፈውን አንብቦ በማረም ለተባበሩኝ ፣ ለአቶ ጌታቸው ተካልኝ ፣ ለአቶ ሰሎሞን ኃ/ማርያምና ፣ ለአቶ ታመነ ግዛው ፤ ቅዱስ ሩፋኤል ይደግፋቸው ፤ ደግሞም የመጽሐፉን ሽፋን እንደገና ለማሣል ላገዘኝ ለአቶ ብርሃኑ ቅዱስ ኡራኤል ይታደጋቸው ፤ እንዲሁም እንድጽፍ ላበረታቱኝ ለአቶ አበራ ሞልቶት ፣ ለአቶ በቀለ አሳምነው ፣ ለአቶ ጌትነት አየለና ለአቶ ከበደ ኃ/ሥላሴ ፣ ለዶ/ር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህና ለፊታውራሪ ገብረ ሕይወት ለዶ/ር ብርሃኑ ግዛውና ለአቶ በለጠ ዓለሙ ፤ ለአቶ ተገኝወርቅ ውቡና ለመሪጌታ ፀሐይ ደምሰው ደግሞም ለወዳጆቼ በሙሉ ቅዱስ ሱርያኤልና ቅዱስ ሰዳካኤል ይባርኳቸው ፤ እንዲሁም ለሊቀ ካህናት ዓባይነህ አበበና ለሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል ፤ ለመምህር ኪዳነ ማርያም የቆሎ ተማሪ ደራሲ ለቄስ ፀጋዬ ታደለ ፡…

፫ኛ) በተለይም ደግሞ ለቅዱስ ሚካኤል ማህበርተኞቼ በሙሉና ለምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም አባላት በሙሉ ፣ እንዲሁም ለመድኃኔ ዓለም ማህበርተኞች ሁሉ ፤ ለተምሮ ማስተማር አባላት ፤ ደግሞም ለህንጻ ተቋራጭ ለአቶ ተስፋዬ ይፍሩና ለመሐንዲስ ለአቶ ሰሎሞን ወረደ ቃል ፣ ለሊቀ·ዲ/ዲሜጥሮስ ወልዱና ለአቶ መኮንን ኃ/ገብርኤል ቅዱስ ሰላታኤልና ቅዱስ አናንያኤል ከመከራ ሁሉ በክንፎቻቸው ይጋርዷቸው አሜን።



# ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት

የአበው ኢትዮጵያውያን እምነት (ዶግማ) በዘመናዊ አገላለጽ በሚል ርእስ ከክፍል 1 እስከ ክፍል 15 ድረስ ለማንኛውም ሰው ሁሉ በሚገባ ቋንቋና ወደ ሌላ ቋንቋም ለትርጉም እንደሚያመች አድርጌ ከእናት ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ውስጥ ለሕዝብ የሚገቡ ቃላቶችን በመምረጥና በተቻለኝ መጠን ተጠንቅቄ ለማስረዳት ሞክሪያለሁ ።

ክቡራን አንባብያን ስለ ብሔራዊት እናት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ብዙ መናገርና ብዙ መጻፍም ይቻላል ። እስከ ዛሬ ድረስም ከተሊያዩ ሊቃውንት ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል ። ነገር ግን ጊዜ ለመቆጠብና አንባብያንን በማያሰለች ሁኔታ መግለጽ አስፈላጊ በመሆኑ እኔም በአጭሩ ለመግለጽ መንፈሴ አስገድዶኛል ። ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥም በመጠኑ ማስረጃ ጠቅሻለሁ ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል ። አሁንም አንባብያንን ላለማሰነፍ ሲባል በመጠኑ ማስረጃ ሰጥቻለሁ ፣ ማለትም ምሳሌ ከተሰጠ ሌላውን ጥቅስ በቀላሉ ማግኘት እንደሚቻል በማመን መሆኑ አይዘነጋም ።

ቢሆንም ይህንን አጭር የሆነ ጥናት እንዳዘጋጅ ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት የአይሁድና የሌላ ልዩ ልዩ እምነት ተከታዮች የሆኑ በአሜሪካና በአውሮፓ እንዲሁም በእናት ሀገር ውስጥ የሚገኙ የባዕድ ሀገር ዜጐች የእየዩኒቨር ሲቲው ፕሮፌሰሮችና መምህራን ደጋግመው ባቀረቡልኝ ጥያቄ መሠረት መሆኑን እየገለጽሁ ፤ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የተለያዩ የክርስትና እምነቶች ልዩ ት በአጭሩ ከክፍል ፩ ጀምሮማስረዳት እሞክራለሁ ።

# መግቢያ ፤

በዚህ ምርምራዊ በሆነ ጥናት ውስጥ አንባብያን የሚያገኟቸው አረፍተ ነገሮችና ኃይለ ቃላቶች ከዚህ በፊት ከተጻፉት መጻሕፍት በጣም የተለዩ ናቸው ። ማለትም በኢትዮጵያ ፤ በግሪክ ፤ በኢጣሊያ ፤ በጀርመን ፤ በእንግሊዝ፣ በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ ከተጻፉ የትምህርተ መለኮትና የምርምር ወይም የትዮሎጂና የፍልስፍና መጻሕፍት ማለቴ ሲሆን በጥናቴ ውስጥ የተጠቀምኩበት ቋንቋም በጣም ቀላል በሆነና ለሕዝቡ በሚገባ ኢትዮጵያዊኛ ወይም አማርኛ ነው ። የግዕዝ አነጋገር አልተጠቀምኩም ። በተቻለኝ መጠን የግዕዙን ቃላት እየተረጐምኩኝ ነው ያቀረብኳቸው ። ቢሆንም በጥናቱ ውስጥ ያተኰርኩባቸው ፍሬ ሀሳቦች እንደሚከተለው ናቸው ።

## ሀ· ከአምስቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ቀጥተኛ እምነት ውስጥ ፤

1· ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ (ሥጋዌ) ፤
2· ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ፤
3· ስለ ምሥጢረ ቁርባን ፤
4· ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ሲሆን ፤

## ለ· ስለ አምስቱ መሥዋዕተ ኦሪት (ቁርባን) ፤

1· ስለ መሥዋዕተ ላህም (ላም) ፤
2· ስለ መሥዋዕተ ጠሊ (ፍየል) ፤
3· ስለ መሥዋዕተ ርግብ ፤
4· ስለ መሥዋዕተ በግዕ (በግ) ፤
5· ስለ መሥዋዕተ ሐሪጽ (ዱቄት) ፤

ይህም የመጨረሻው መሥዋዕት ነው ፤ ከንጹህ ስንዴ የተሠራ የቂጣ በዓል ከወይን ፍሬ ጭማቂ ጋር ፤ ይህ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ሐሙስ (በሐሙስ ቀን) ከሐዋርያት ጋር ባርኮ እውነተኛ ሥጋውና ደሙ አድርጐ አዲስ ሥርዓት የሰጠን ፤ ዝርዝር ፍሬ ነገሩን በጥናቱ ውስጥ በክፍል ፲ ላይ ፤ ይመልከቱ ።



## ሐ· የኢትዮጵያ ተዋሕዶ የምትቀበላቸው ፤ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች ፤

1· በ325 ዓ·ም· በአርዮስ ላይ ፤
2· በ381 ዓ·ም· በመቅዶንዮስ ላይ ፤
3· በ431 ዓ·ም· በንስጥሮስ ላይ ፤

## መ· የኢትዮጵያ ተዋሕዶ የማትቀበላቸው፣ በሲኖዶስ ስም የፖለቲካ ውሳኔዎች ፤

1· በ451 – 1014 ዓ·ም· ኦርቶዶክስ የተባለበት ዘመን ፤
2· በ1014 – 1054 ዓ·ም· ካቶሊክ የተባለበት ዘመን ፤
3· በ1517 – 1521 ዓ·ም· ፕሮቴስታንት የተባለበት ዘመን ፤

ይሁን እንጂ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የፖለቲካ ውሳኔዎች መሆናቸው የታወቀ ቢሆንም ከሌላው ልዩነቱን ለማሳወቅ በዚህ ጥናት ውስጥ ተጠቅሰዋል ፤ ይህም እንደ ማወቅ አይቆጠርም ።

## ሠ· በእናት ኢትዮጵያና በምሥር (ግብጽ) የሚገኙ ፒራሚዶችና ሌሎች በጣም አስደናቂ የሆኑ ሕንጻዎች ማን እንደሠራቸው የሚናገር ፤

ክፍል ፲፪ እና ፲፫ የሚያስረዱት ከግብጽ በፊት በእናት ኢትዮጵያ ውስጥ ፱ የፒራሚድ ከተሞች መኖራቸውንና ማን እንደ ሠራቸውና ለምን እንደተሠሩ የሚያስረዳ ፤ እንዲሁም የግብጽ ፒራሚዶች እንዴት እንደ ታነጹ የሚገልጽ ሲሆን ፤ የአክሱም ሐውልቶችና የላሊበላ ቤተ መቅደሶች ደግሞም ሌሎች የተደበቁ ሕንጻዎች በማን እጅ እንደ ተገነቡ በመጠኑ የሚያብራራ ነው ። ከዚህ ላይ የገባው ምንም ቢሆን የእምነት ይዘት ቢኖረውም ነገር ግን ለሕዝብ የማስተዋወቀው በታሪክነቱ ነው ። ክፍል ፲፬ እና ፲፭ ደግሞ የተጻፉት በኋላ ሲሆን ሙሉ በሙሉ የሃይማኖት ኃይለ ቃል ያለበት ነው ።

# መ ቅ ድ ም ፤

ይህ የሃይማኖት ወይም የእምነት መጽሐፍ ከዚህ በፊት በተለያየ ቋንቋ ከተጻፉ መጻሕፍት በጣም የተለየ ነው ፤ ምክንያቱም በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱ እምነቶች ታሪካቸው ከእነአመጣጡ በሚገባ የሚገልጽ ከመሆኑም በላይ ራሱ ባለቤቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሰረታትና ሐዋርያት፣ ሰብዓ አርድዕት ፣ በኋላም ፫፻፲፰ ሊቃውንት ወይም አባቶች ባፀኗት ከአንዲት ቅድስት ተዋሕዶ እንዴትና ለምን እንደ ተለዩ ከመነሻ ምክንያቱ ጭምር በሚገባ የሚያስረዳ ስለሆነ ነው ።

ይሁን እንጂ ጥናቱ በ፲፰ት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ክፍል ፩ አንድ የሚያብራራው ከጥንት በአምልኮተ ፀሐይ ጀምሮ እስከ ብሉይ ኪዳን ድረስ እንዲሁም ደግሞ ለዘለዓለም የማይጠፋ እውነተኛ ፀሐይ ስለ መድኃኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስረዳ ነው ፤ ክፍል ፪· ፫· ፬· ደግሞ ስለ ምስጢረ ተዋሕዶ በአጭሩ የሚተነትን ሆኖ በተለይ ደግሞ ከጥንት አባቶቻችን ሲያያዝ የመጣ ትርጓሜ ያለበት ፣ መምህሬ የኔታ የኋላእሸት እንደነገሩኝና የራሴም ልዩ አስተያየት ታክሎበት ስለ ምሥጢረ ተዋህዶ የሚናገሩትን ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፱ እና ፲ ላይ ከአይሁዶች ጋር የተደረጉትን የክርክር ጥያቄና መልስ ያለበት ትርጉም የያዘ ሲሆን ፣ በተለይ ደግሞ ዕውር ሆኖ ስለተወለደው ስም አማን አምኖስ መሆኑን የሚገልጽ አዲስ ምሥጢር እናገኝበታለን ።

እንዲሁም ደግሞ ክፍል ፭ት የእምነት ልዩነቶች እንዴት እንደ ተፈጠሩ እንደ መግቢያ በር ሆኖ የሚያስረዳን ሲሆን ክፍል ፮ት ስለ የእምነት መሰረት ተዋሕዶ <u>1–33–451</u> ዓ·ም· ነው ። ክፍል ፯ት ስለ አርቶዶክስ <u>451–1014</u> ሲሆን ክፍል ፰ት ደግሞ ስለ ካቶሊክ 1014–1054 ዓ·ም· ነው ። እንዲሁም ክፍል ፱ ስለፕሮቴስታንት <u>ከ1517–1521</u> ዓ·ም· ሲሆን ፣ ደግሞ ክፍል ፲ ስለ ምሥጢረ ቁርባን በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ብቻ ነው ። ክፍል ፲፩ ስለ ቅዱስ ቁርባን ሥራ በአውሮፓና በሌላው ዓለም እንዴት እንደሚፈጸም የሚያስረዳን ነው ።



ስለዚህ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለጹትን ዝርዝር ፍሬ ሀሳብ በጥናት ውስጥ መረዳት የሚቻል ቢሆንም ፣ ነገር ግን ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ሌሎች የዓለም ሕዝቦች ፣ የአክሱም ሐውልቶችና የላሊበላ ቤተ መቅደሶች እንዲሁም የምስር ወይም የግብጽ ፒራሚዶችና ሐውልቶች ሌሎችም በጣም አስደናቂ ሥራዎችን እንዴት እንደ ተሰሩ ማን ሰራቸው እያሉ በቃልም በጽሑፍም የጥያቄ ምልክት ሲያቀርቡ በማየቴና በመሥማቴ ነገሩ በእኔም አእምሮ ይወጣ ይወርድ ስለነበር መቼ እንደምገልጸው አመቺ የሆነ ጊዜ እፈልግ ነበር ። ስለዚህ በ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ነሐሴ ፲፫ ቀን ዓርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥቢያ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ስሔድ በደረሰብኝ የመኪና አደጋ ምክንያት ከፍ ብሎ በመጠኑ እንደ ተጠቀሰው ሰዎች ለማወቅ የሚፈልጉትን ምሥጢር በጥቂቱም ቢሆን ለመግለጽ እንድችል ለዘለዓለም የማይጠፋ ፀሐይ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በመጠየቅ ከግብጽ በፊት የተሠሩ ፱ ፒራሚዶችንና ፲፪ ከተሞችን እንድገልጽ ስለተፈቀደልኝ ሰዎች ለመቀበል አስቸጋሪ ቢሆንባቸውም በክፍል ፲፪ እና ፲፫ ላይ ፒራሚዶቹና ሐውልቶቹ እንዲሁም ቤተ መቅደሶቹ ለምን እንደተሠሩና ማን እንደሠራቸው በሚገባ የተብራራ ስለሆነ በጽሞና እንድታነቡት በትህትና አሳስባለሁ ።

እስከዛሬ ድረስ እንደሚታወቀው ሁሉ የግብጽ ኮብቲክ ቤተ ክርስቲያን እምነት እንደ ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር አንድ እንደሆነ ነበር የሚታመነው ፣ ስለዚህ በሥርዓትም ሆነ በእምነት ከኢትዮጵያ ተዋሕዶ ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ መሆኑን የሚያስረዳ በክፍል ፲፬ ላይ ይመልከቱ ። ይሁን እንጂ ከፈጣሪያችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ቀጥሎ በዓለም ውስጥ አምኖ የተጠመቀ የመጀመሪያው ሰው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወይም በትክክለኛ ስሙ መልከ ጼዴቅ ፪ኛ ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ደግሞ በክፍል ፲፰ ላይ ነው ።

የነበረ የሚኖር ሕያው እግዚአብሔር
ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን ፣
አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

እናገኘዋለን ፣ ይኸውም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ለካህናትና ለሕዝብ በገሀድ (በግልጽ) ያስረዳበትና ያሳየበት የምስጢረ ተዋህዶ ቁልፍ ነው ። መድኃኒታችን ኢየሱስም በቤተ ሳይዳ በሚገኘው የአይሁድ ምኩራብ (መስጊድ) አጠገብ ሲያልፍ በመንገድ ጠርዝ (ዳር) ላይ ተቀምጦ የሚለምን ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን የ፳፫ ዓመት ጐልማሣ ሰው አየ ። ወዲያውኑ ሌሎች ደቀ መዛሙርቱና ወንድሞቹ ሐዋርያት አምላካችንና መምህራችን ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ የተወለደው በማን ኃጢአት ነው ? በራሱ ነውን ወይስ በወላጆቹ ? ብለው ጠየቁት ፤

ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ከዚያ በፊት ሌሎች ዓይነ ስውሮችና አካለ ስንኩሎች ሳያዩ ቀርተው ነውን ? ከእርሱ በፊት ካዩዋቸው ዓይነ ስውሮች በጣም የተለየ ስለሆነባቸው ነው በመገረም የጠየቁት ። ለሐዋርያትም እንዳስደነቃቸው ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው ከእርሱ በፊት እንደነበሩ ዓይነ ስውሮች ሣይሆን ነገር ግን በዘመናችን በእየሆስፒታሎቹ ጉድ ተብለው እንደሚወለዱ የባሰና የከፋ ጉድ ነው ። ይኸውም የዓይኖች ቅንድብና የአፍንጫ ቅርጽ የሌለው አፍንጫው ከአፉ ጋር የተያያዘ በአፉ የሚተነፍስ የተዳመጠ መጅ የሚመስል ደረቅ ግንባር ነው ። ቢሆንም እንደ አራት ዓይና ጐሹ ዓይነ ልቡናው የሚያበራ አእምሮው በምስጢረ ተዋሕዶ የተሞላ ሰው ነበር ።

# <u>ክፍል ፫</u>

## <u>በማይታበል ቃሉ የመድኃኒታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ መልስ ፤</u>

## <u>ሐ· የእኔ አምላክነት በእርሱ ይታወቅ ዘንድ ነው ፤</u>

የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው የሆነ ጌታችንና ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ለሐዋርያት የሰጣቸው መልስ ይህ ሰው ዕውር



ሆኖ የተወለደው እርሱም አልበደለም ፣ በወላጆቹም ኃጢአት አይደለም ፣ ነገር ግን በአብና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የእኔም ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆን በተዋሕዶ በእርሱ ይገለጥ ዘንድ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ። ስለዚህ ይህ ሰው ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ያደረግነው የሚል ነበር ።

## <u>፩· የዚህ ዓለም ብርሃን ማን ነው ፤</u>

የዚህ ዓለም ብርሃን ለጊዜው አጭር የሆነ መልስ ፀሐይ ነው ይባል ይሆናል ። ነገር ግን ፀሐይ ዘለዓለማዊ ብርሃን አይደለም ጊዜያዊ የሆነ ብርሃኑም የራሱና የባሕርዩ አይደለም ።

አስቀድሜ በመጀመሪያ በክፍል አንድ በመጠኑ እንደገለጽኩት ሁሉ የዚህ ዓለም ብርሃን ፣ ብርሃኑም የራሱና የባህሪዩ የሆነ ለዘለዓለም የማይጠፋ ብርሃን እውነተኛው ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚለው መልስ እውነት ነው ።

ስለዚህ ፀሐይም ሆነ ጨረቃ ሌሎችም ከዋክብት ብርሃናቸውን የሚያገኙት ለፍጥረቱ ሁሉ መገናኛ የኃይል ሁሉ ምንጭ ከሆነው ለዘለዓለም የማይጠፋ ፀሐይ ከመድኃኒታችንና ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በማንም ዘንድ የማይካድ ሐቅ ነው ።

## <u>፪· ለዘለዓለም የማይጠፋ ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤</u>

መድኃኒታችን ኢየሱስም ዕውር ሆኖ ስለተወለደው ሰው ከደቀመዛሙርቱ ጋር ጥቂት ጊዜ ከተነጋገረ በኋላ እኔ የዚህ ዓለም ብርሃን ነኝ ፣ ማንም ሰው ሥራ ሊሠራበት የማይችል ጨለማ ይመጣልና ብሎ መለኮት <u>የተዋሐደው</u> የሰው ልጅ ምራቁን ከመሬት ላይ እንትፍ ብሎና በእጁ ለውሶ ጭቃ ካደረገው በኋላ ዕውር ሁኖ የተወለደውን ሰው ደረቅ ግንባርና ልሙጥ ፊት በተለወሰው ጭቃ የሰው መልክ ቅርጽ ካበጀለትና በጣም ቆንጆ መልክ መልካም አድርጎ ከሳለው በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ ምሳሌና አርአያ

ይሆናቸው ዘንድ ቤተ ሠሊሆም በተባለው የፀበል ውሃ ታጠብና ዓይንህ ይበራልሃል ወዲያውኑ ታያለህ ብሎ በአምላካዊ ቃሉ አዘዘው ።

ዕውር ሆኖ የተወለደውም ወጣት የፈጣሪውን ትእዛዝና ቃል ባለመጠራጠር አምኖ በመቀበል ወደ ቤተ ሰሊሆም መጠመቂያ በፍጥነት ገሠገሠ ከቤተ ሳይዳ እስከ ቤተ ሰሊሆም ያለው ርቀት ዕውር ሁኖ በተወለደው ሰው እድሜ እንደ አጋጣሚ ፰፭ ኪ·ሜ· ነበር ። ዕውሩም ወደ መጠመቂያው በደረሰ ጊዜ ልብሱን አወላለቀና ገብቶ ተጠመቀ አምላኩ እንዳለው ዓይኖቹም በሩለት ፤ በደስታ ተውጦ ወደ ቤቱ ተመለሰ ። በግራ ጆሮው ላይ አንድ የሆነ ምልክት ነበረውና እርሱ ነው አይደለም በማለት የመደነቅና የመገረም ንትርክ በሰዎች መካከል ተፈጠረ ።

## ፫· በአይሁድና በአምኖስ መካከል የነበረው ክርክር ፤

በአምኖስና በጐረቤቶቹ መካከል የሞቀ ክርክር ተጀመረና ጐረቤቶቹ ከሁለት ተከፍለው ይህ ሰው በምኩራብ አጠገብ ተቀምጦ ሲለምን የነበረ አይደለምን ? አሉ ፤ ሌሎቹ ደግሞ ይመስለዋል እንጂ እርሱ አይደለም ሲሉ ራሱ አምኖስ እኔ ነኝ በፊት በመስጊድ ተቀምጬ ስለምን የምታውቁኝ በማለት ነገሩን አፈነዳላቸው ።

ሰዎቹም ንግግራቸውን በመቀጠል ዓይኖችህ እንዴት ተከፈቱልህ የማንስ ኃይል አበራልህ ብለው ጠየቁት ፤ እርሱም መልሶ በዓይናችሁ እያያችሁ የማታስተውሉት በመካከላችን የሚገኝ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ፤ ማለትም ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ፍጹም የሰው ልጅ የሆነ ፤ የዚህ ዓለም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይኖቼን አበራልኝ አላቸው ። እነርሱም መልሰው ዓይኖችህን እንዴት እንደ አበራልህ አብራራልን አሉት ።

እርሱም መልሶ የሰው ዘር ሁሉ አባት የሆነው የሁላችንም አባት አዳምን እንዴት እንደ ፈጠረው የምታውቁ ይመስለኛል ፤ አፈሩን ጭቃ አድርጎ በሚገባ አዋህዶ በራሱ መልክና ቅርጽ አስተካክሎ ከፈጠረው በኋላ አራቱን ባሕሪያተ ሥጋና ሦስቱን ባሕሪያተ ነፍስ አዋህዶ ከሠራው በኋላ ከራሱ ባሕሪይ የምትገኝ የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት ፤ አዳምም



የሚያምር መልከ መልካም ፣ የሚያስብና የሚናገር ፍጹም ሰው ሆኖ ተራመደ የምትረዳውም ሴት አብሮ ፈጠረለት ፣ ዘፍጥ· ም· ፩ ቁ· ፳፮–፳፱ ።

አራቱ ባሕሪያተ ሥጋ ፣ ሦስቱ ባሕሪያተ ነፍስ ፣ ማለት ምን ማለት ይሆን ? አራቱ ባህሪያተ ሥጋ ማለት መሬት ፣ ውሃ ፣ እሳትና ነፋስ ሲሆኑ ፣ ሦስቱ ባሕሪያተ ነፍስ ማለት ደግሞ ሕያዊት ፣ ለባዊት ፣ ነባቢት ናቸው ። መሬትን ከዱላሌብ ፣ ውሃን ከናጌብ ፣ ነፋስን ከአዜብ ፣ እሳትን ከኮሬብ አምጥቶ ሦስቱን ባሕሪያተ ነፍስ ከራሱ ባሕሪይ ነስቶ ከአዳም ባሕሪይ ጋር አዋህዷቸዋል ።

ስለዚህ ዘለዓለማዊ የሆነ ሕያው አምላክ አራቱን ባሕሪያተ ሥጋና ሦስቱን ባሕሪያተ ነፍስ ከአዳም ሰውነት ጋር በማዋሐድ አባታችን አዳም የሚያስብ ትዕግስተኛና አዋቂ ሩኅሩህ ቸር ይቅር ባይ የሚያምር መልከ መልካም ቆንጆ ግርማ ሞገስ ያለው የ፳፭ አመት ጐልማሳና የሚያነቃ ልሳን ያለው ፍጹም ሰው ሆኖ ተራመደ አምስቱ አእማደ ምስጢር የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንድምታ ትርጓሜ ፩ሺ፱፻፺ ገጽ ፳፪ ላይ ተመልከት ።

አምኖስ ለአይሁድ ሽማግሎችና ለጠየቁት ሕዝቦች የሰጠው መልስ ፣ እንደ አባታችን አዳም አንድ ብሎ የፈጠረው ባይሆንም ነገር ግን እንደ አዳም አፈጣጠር ተመሣሣይና ተቀራራቢነት ስላለው ነው ። ከዚህ በላይ የአዳምን ታሪክና አፈጣጠር በምሕጻረ ቃል የገለጽኩት ፣ ማለትም ዕውሩም አዳምም አፈሩን ጭቃ አድርጎ ስለ ሠራቸው ነው ። የአምኖስ መልስ የማይታየው ዓለምና የሚታየው የዚህ ዓለም የማያቋርጥ ብርሃን ፤ የኃይልና የፍጥረቱ ሁሉ ምንጭ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት የተወሐደው የሰው ልጅ ምራቁን ወደ መሬት እንትፍ ብሎ በምራቁ አፈሩን ጭቃ አድርጎ በልሙጥ ግንባሬ ላይ ሥሎ የሰው መልክና ቅርጽ ከአበጀልኝ በኋላ ቤተ ሰሊሆም ወደ ተባለ መጠመቂያ ሂድና ታጠብ አለኝ ። እኔም ሄድኩና በመጠመቂያው ውስጥ ገብቼ ታጠብኩኝ ዓይኖቼም ተከፍተው በሩልኝ የሚል ነበር ። እነርሱም መልሰው የአይሁድ ሰላዮች ነበሩና ሙሉ ቅርጽህን ሠርቶ የዓይኖችንህ ብርሃን የሰጠህ ሰው አሁን ወዴት ሄደ ብለው ጠየቁት ፤ አምኖስም በቁጣ ቃል ወዴት እንደ ሄደ አላውቅም አላቸው ።

## ፬· የፈሪሳውያን ጥያቄና የአምኖስ መልስ

ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው ስም አምኖስ መሆኑን የሚናገረው መጽሐፍ ደግሞ የሚገኘው በ፫፻፶ ዓ·ም· የተጻፈ የእጅ ረቂቅ በዋልድባ ውስጥ አምርሐ (አብርሃ) ደጋ በተባለ ስፍራ በአስደናቂው ሕንጻ ውስጥ ነው ።

የእናት ሀገራችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ እምነት በሕገ ኦሪት በብሉይ ኪዳን ሕግ ነበር ፤ ነገር ግን ከብሉይ ኪዳን ሕግ ወደ ሐዲስ ኪዳን ሕግ የተለወጠበት ዘመን ከ፪፻፶ና ፫፻ ዓ·ም· ነው ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ እምነት በሕገ ኦሪት በብሉይ ኪዳን መሆኑ ቀርቶ በሐዲስ ኪዳን ሕግ መሆኑንና ሌሎችም በጣም ጠቃሚ የሆኑ አዋጆችን የሚገልጸው የብራና መጽሐፍ የሚገኘው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አስደናቂ ሕንጻ ውስጥ ነው ። ያልተበረዘና ያልተከለሰ የመጀመሪያውን ጽሑፍና ቃል የያዙ መጻሕፍትም የሚገኙት ከዘጠኙ ሕንጻዎች ውስጥ በአንዱ በዚህ በተጠቀሰው ሕንጻ ውስጥ መሆኑን ለአንባቢያን እጠቁማለሁ ።

ሌሎች ሀገሮች ወደ ክርስትና እምነት የገቡት ከአረማዊነት ሲሆን ነገር ግን ኢትዮጵያ በቀጥታ ከሕግ ወደ ሕግ ነው የተሸጋገረችው ። ማለትም ከሕገ ኦሪት ወደ ትንቢቱ መፈጸሚያ ወደ ሕገ ወንጌል ነው ፤ ይህም ለኢትዮጵያው ያንና ለጥቁር ሕዝቦች በሙሉ ከፍተኛ ኩራት ነው ።

የአይሁድ ሰላዮች አማን አምኖስን ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት መድኃኒ ታችን ኢየሱስ መለኮት የተወሐደው ምራቁን ከአፈር ጋር አዋሕዶ ዓይኑን ያበራለት ቀኑ ቀዳሚት ሰንበት ስለነበረ ነው ። ፈሪሳውያን ደግሞ ዓይኑ እንዴት እንደ በራለት ጠየቁት ፤ አምኖስም ኢየሱስ የተባለው የዚህ ዓለም መድኃኒት መንፈስ ገልጾለት የዚህ ዓለም አለ በሌላው ዓለም ነፍስ ያለው ፍጥረት ስለሌለ ፤ ምራቁን በጭቃ አዋሕዶ ዓይኖቼን ቀብቶ የሰው መልክ ቅርጽ አበጅቶ በሰሊሆም ፀበል ታጠብ አለኝ እኔም ሄጄ ታጠብሁ ዓይኖቼም ተከፈቱልኝ አላቸው ።



## ፭· በፈሪሳውያንና በአይሁድ መካከል መለያየት ተፈጠረ፤

ከፈሪሳውያን አብዛኞቹ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አጉረመረሙ አሴሩበትም ይህ ሰው ቀዳሚት ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚ አብሔር የተላከ ነቢይ አይደለም ሲሉ ፤ የአይሁድ ሽማግሌዎች ደግሞ ይህ ሰው ከአምላክ የተላከ ነቢይ ባይሆን ኑሮ አንዳችም ነገር ማድረግ ባልቻለም ነበር ነገር ግን ብዙ ተአምራቶችን ሲያደርግ በዓይናችን እያየን ነው ። በዚያውስ ላይ ኃጢአተኛ ሰው በልሙጥ ደረቅ ግንባር ላይ በምራቁ ጭቃን አዋሕዶ ቀብቶ የሰውን ዓይን መፍጠር ይችላልን ? ስለዚህ ይህ ሰው በእውነት ከእግዚአብሔር የመጣ ነቢይ ነው አሉ ።

ፈሪሳውያንም መልሰው ዕውር ሆኖ የተወለደው አማን አምኖስን ዓይንህን አብርቶልሃልና አንተስ ስለሱ ምን ብለህ ታምናለህ ? ብለው ጠየቁት እርሱም መልሶ ዓይኔን ያበራልኝ መሆኑን እኮ እናንተም እየመሰከራችሁ ነው። አለማመናችሁ ግን አስገርሞኛል ካለ በኋላ በፈቃዱ የሰውን ሥጋ የተወሐደ የዚህ ዓለም ብርሃንና የሰው ዘር ሁሉ መድኃኒት የሆነ እውነተኛ ነቢይ ነው ብዬ አምናለሁ አላቸው ።

ስለዚህ ፈሪሳውያን ደግሞ ዕውር ሆኖ መወለዱን ስላላመኑ የዕውሩን ወላጆች አስጠርተው ዕውር ሆኖ ተወለደ የሚባለው ልጃችሁ ይህ እውነት ነውን ? ብለው ጠየቋቸው ።

ወላጆቹም መልሰው ይህ በእውነት ልጃችን ነው ከመወለዱም ጀምሮ ዕውር ሁኖ እንደ ተወለደ እናውቃለን ። አሁን ግን ዓይኑን ማን እንዳበራለት አናውቅም አሉ አይሁድን ስለፈሩ ካዱ እንጂ ዓይኑን ያበራለት የዚህ ዓለም ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በሚገባ ያውቃሉ ። ነገር ግን ልጁ የ፳፭ አመት ጐልማሳ ነው ስለ ራሱም አጣርቶ መናገር ይችላልና ራሱን ጠይቁት ብለው በድጋሚ አረጋገጡ ።

## ፮· የአማን አምኖስና የአይሁድ ፈሪሳውያን የሕቅታ መልስ ፣

የአይሁድ ፈሪሳውያንም መልሰው ዕውር የነበረውን ሰው አማን አምኖስን ለሁለተኛ ጊዜ ጠርተው ይህ ዓይንህን የከፈተልህ ሰው ቀዳሚት ሰንበትን አያከብርምና ከአምላክ ዘንድ አይደለም ፣ ኃጢአተኛ ሰው መሆኑንም እኛ እናውቀዋለንና ለእግዚአብሔር ምሥጋና አቅርብ አሉት ፣ እርሱም መልሶ ኃጢአተኛ ሰው መሆኑን አላውቅም ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ አውቃለሁ ይኸውም ዕውር እንደ ነበርኩና በእርሱ ኃይልም የዓይኔን ብርሃን እንዳገኘሁ አላቸው ።

ፈሪሳውያንም መልሰው ለሦስተኛ ጊዜ ምን አደረገልህ ብለው ጠየቁት፣ አማን አምኖስም ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ነግሬያችሁ ነበር አልተቀበላችሁኝም በዓይናችሁም የሚሠራውን ተአምራት ሁሉ እያያችሁ አላመናችሁም፣ እንደገና ለምን መስማት ፈለጋችሁ እናንተም ደግሞ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ፈለጋችሁን ? አላቸው ። እነርሱም እንዲህ ብለው ሰደቡት ፣ አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ሁን እኛ ደግሞ የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን አምላክም ከሙሴ ጋር በሲና ኮረብታ ላይ ቃል በቃል እንደ ተነጋገረው እናውቃለን ይህ አንተ የምትመሰክርለት ግን ከወዴት እንደ መጣ እናውቅም አሉት ።

አማን አምኖስም በምራቁ ከጭቃ አዋሕዶ ዓይኔን ያበራልኝ መሆኑን እያያችሁ አለማመናችሁ ይህ ዕፁብ ድንቅ ነው ፣ እኛ ደግሞ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ኃጢአተኞችን እንደ ማይሰማቸው በሚገባ አጣርተን እናውቃለን ፣ አምላክም ፈቃዱን የሚፈጽምና ድንቅ የሆኑ ሥራዎቹን በዓይኑ አይቶ የሚያምን ሰው ቢኖር እርሱን በፍጥነት ይሰማዋል ። እንደ እናንተ ያለ እያየና እየሰማ የማያምን አፉ የእባብ መርዝን የተሞላ ምላሱ የሚያቃጥል ሰው ቢኖር ግን እሳቱ ለዘለዓለም ወደ ማይጠፋ ገሀነም ይጥለዋል ።

ደግሞም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ከእናቱ ማኅፀን ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በልሙጥ ግንባር ላይ ዓይንን የፈጠረ ኃይል ታይቶና ተሰምቶ



አያውቅም ይህ የምታዩት ፍጹም ሰው በፈቃዱ የሰውን ሥጋ የተወሐደ ዘለዓለማዊ የብርሃን አምላክ ባይሆን ኖሮ እኔን አስቀድማችሁ እንደ ምታውቁኝ የዓይኔን ብርሃን መስጠት ባልቻለም ነበር አላቸው ።

የአይሁድ ፈሪሳውያን መልሰው አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተሞልተህ የተወለድህ መሆንህን እያወቅን ተመልሰህ እኛን ታስተምረናለህን ? ብለው ከምኵራብ (ከመስጊድ) ገፍትረው ወደ ውጭ አወጡት ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስም እነርሱ ሳያዩት በመካከላቸው ነበረና ወዲያውኑ ዕውር የነበረውን ሰው አንተ ዘለዓለማዊ ሕያው በሆነ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን ? አለው አማን አምኖስም መልሶ አቤቱ አምንበት ዘንድ የምትለኝ ሰው እርሱ ወዴት አለ ብሎ መለሰለት ።

የአዳምን ሥጋ በራሱና በአባቱ ፈቃድ የተወሐደ ኢየሱስ ክርስቶስም መልሶ በዓይንህ በፊትህ ቁሜ የምታየኝና ከአንተም ጋር የምነጋገረው እርሱ እኔ ነኝ ብሎ እውነቱን ነገረው ዕውር የነበረውም ሰው አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ሆይ አምናለሁ በማለት በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደለት ።

መድኃኒታችንና ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስም እኔ ወደዚህ ዓለም የመጣሁት የማያዩ ሰዎች ያዩ ዘንድ የሚያዩት ደግሞ እያዩ እንዳያስተውሉ ይሆኑ ዘንድ ለፍርድ ነው ሲል የፈሪሳውያን ሰላዮች አብረውት ነበሩና እኛ ዕውራን መሆናችን ነውን ? አሉት እርሱም መልሶ ዕውራንስ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር ፣ ስለዚህ ለኃጢአታችሁ ስርየት የላትም አላቸው ፣ የዮሐንስ ወንጌል ም· ፱ ቁ· ፩—፵፩ ላይ ተመልከት ።

# ክፍል ፬

## አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት በባሕርይ በሕልውና አንድ አምላክ ናቸው

## ፩· ትክክል የሚሆኑ በመለኮት አንድም ሦስትም ናቸው

በስም በግብር በአካል ሦስት ሲሆኑ ፣ በባሕርይ በሕልውና በመለኮት አንድና ትክክል የሚሆኑ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ናቸው ። አብ

ወይም የኢኮኖሚ አውታር ምክንያት ብዙ የሆነ ገንዘብና ብዙም የማያቋርጥ የገቢ ምንጭ ስላላቸው አሁንም ቢሆን በቀላሉ የሚበገሩ አይደሉም ።

ስለዚህ የቅርብና የሩቅ አባሎቻቸውን በተለያየ ጥቅምና በምቾት ስለያዟቸው ብዙ ደጋፊዎች እንዳሏቸው የማይካድ እውነት ነው ። ምክን ያቱም ዓለም የሚገዛው ለጥቅምና ለገንዘብ ስለሆነ ነው ። ኃያላን የሚባሉ የዓለም መሪዎች አብዛኞቹ በገንዘብ ኃይል በእነርሱ ቁጥጥር ስር ናቸው ።

የስለላ ድርጅታቸውም አሉ ከሚባሉ የስለላ ድርጅቶች ከሲ አይኤና ከሞሳድ በተሻለ ሁኔታ በመላ ዓለም መዋቅሩ የተዘረጋ ነው ። ያውም በጣም አደገኛ ሳይታወቅ በሃይማኖት ሽፋን ሆኖ የአሜሪካኖችና የአይሁዶች የስለላ ድርጅትም ቢሆን በጣም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን የሚያገኘው ከካቶሊክ የስለላ ድርጅት መሆኑ የማይካድ እውነት ነው ።

ቀደም ሲል የነበረው የስለላ ድርጅት ማለትም ማሦኒክ ቁጥር ፫ በመባል የሚታወቀውና በዓለም የመሪዎች መልማይ የሆነና በአመጽ በግፍ የተሞላ የዚህም ድርጅት መሥራችና አባል የሆኑ የካቶሊክ ሃይማኖት መሪዎች መሆናቸው የታወቀና የተረጋገጠ ቢሆንም የባሰው ደግሞ በዘመ ናችን አዲስ አለም በመባል የሚታወቀው ወይም በራእየ ዮሐንስ በም· ፲፫ ቁ· ፲፮–፲፱ ላይ እንደተገለጸው አውሬ የ666 መሥራችና አባላትም የካቶሊክ ሃይማኖት መሪዎች መሆናቸው ነው ።

ስለዚህም ነው በኢትዮጵያ የአንድ ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ እንኳን የማታህለው የቫቲካን ትንሽ ከተማ በመንግሥትነት እንድትታወቅና ራሱን እንደቻለ እንደ አንድ ሀገር እንድትጠራ ያደረጓት ፤ በዓለምም እንደ ማንኛውም ሀገርና መንግሥት ሁሉ አምባሳደሮችንና ቆንስሎችን ትሾማለች በአጸፋውም የሌላውን ሀገር አምባሳደርና ቆንስልም ትቀበላለች ይህች ሀገር መንግሥት ናት ወይንስ የሃይማኖት ድርጅት ?

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህች በጣም ትንሽ የሆነችው ከተማ የምትታወ ቀውና የምትጠራው እንደ አንድ መንግሥት ነው ። መንግሥትም ከሆነች ማንኛውም የአለም መንግሥት ሁሉ እንደ ሚፈጽመው የአመጽና የግድያ



ሥራ ሁሉ ትፈጽማለች ማለት ነው ። ይህ የማይካድ እውነት ነው የራሷንም አባላት ሳይቀሩ በሞት ቀጥታለች እንዳልቀጥራቸው ብዙ ናቸው ፤ የታወቁ ስለሆነ ታሪክ ይቁጠራቸው ።

በኢጣሊያ ሀገር ሮም ውስጥ ፪ት መንግሥታት አሉ ማለት ነው ፤ አንደኛው ዓለም አቀፍ የሆነ የቫቲካን ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ የኢጣሊያ መንግሥት ነው ። በሮም ከተማ ውስጥ በፖሊስ ሞተር ሣይክል የሚታጀበው ከፕሬዚዳንቱና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ይልቅ ፓፓው ነው ፤ ምክንያቱም በሃይማኖት አባትነቱ አክብረው ሣይሆን በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበላይነቱን በማመን መሆኑ አይካድም ።

ከዚህ ቀጥዬ ደግሞ በእየጊዜው ከካቶሊክ ተገንጥለው ሉተርን ጨምሮ በስማቸው የሃይማኖት ድርጅትን የመሠረቱና የትውልድ ሀገራቸውን ሳይቀር በዝርዝር አቀርባለሁ ። ቀደም ሲል ከላይ በክፍል ፯ ውስጥ ከተወሕዶ፣ ከኦርቶዶክስ ፣ ከካቶሊክ በስተቀር ሌሎች ክርስቲያን ነን የሚሉ ሁሉ ብዛት ቢኖራቸውም ከቁጥር ውስጥ እንደማይገቡ መግለጼን አስታው ሳለሁ ። አሁንም ቢሆን ጻድቃን ፣ ሰማዕታት ፣ መላእክት ፣ ንጽሕት ድንግል የአምላክ እናት የሆነች ቅድስት ማርያምን ጭምር እያማልዱም ከማለት በስተቀር በቤተ ክርስቲያን በኩል የራሳቸው የሆነ ባሕልና ሥርዓት ስለሌላቸው ታሪክ ስለሆነ እዚህ ላይ ጠቀስኳቸው እንጂ ከቁጥር ውስጥ አይገቡም ከተገነጠሉበት በካቶሊክ ሥር ናቸው ። እነዚህም እንደሚከተሉት ናቸው ።

፩· ሉተር ሉተራኒዝም ፣ <u>ጀርመን ፣</u>

፪· ፍሊጅ ሚላቶን ሚላቶኒዝም ፣ <u>ጀርመን ፣</u>

፫· ሲመንስ ሜኖኒዝም ፣ <u>ዴንማርክ ፣</u>

፬· ኖክስ ፕሬዝቪተርያኒዝም ፣ <u>ስኮትላንድ ፣</u>

፭· ክራንሜር አግሊካኒዝም ፣ <u>ኢንግላንድ ፣</u>

፮· ስሚዝ ባቭቲዝም ፣ <u>ኢንግላንድ ፣</u>

፯· ዝውንጄል ዝውንጄሊዝም ፣ <u>ፍራንስ ፣</u>

፰· ግሬቬል አንባቪቲዝም ፣ <u>ስዊዝ</u>

፱· ካልቪን ካልቪንዝም ፣ <u>ስፔን ፣</u>

ከዚህ በላይ ከቁጥር ፩ እስከ ፱ ድረስ የተጠቀሱት የሥልጣን ጥመኞች ከእናታቸው ከሥልጣን ሱሰኛዋ ከካቶሊክ የተገነጠሉት እውነት ፍለጋና ትክክለኛ የሆነ የሃይማኖት ድርጅት ለመመሥረት ሳይሆን ነገር ግን ከላይ በክፍል ፱ እንደተጠቀሰው ሁሉ የካቶሊኮች የባርነት ቀንበር ስለፀናባቸውና የእየሀገሮቻቸውም ነገሥታት ባቀረቡላቸው ጥሪ መሠረት መሆኑ የታወቀ ነው ። የሃይማኖት ወይም የእምነት ድርጅት ለማቋቋም ቢፈልጉ ኖሮ ድርጅታቸውን በእግዚአብሔር ስም በሰየሙት ነበር ። ነገር ግን ከዘጠኙ አንዱም እንኳን በስመ አምላክ ድርጅቱን የሰየመ የለም ፤ ስለዚህም ነው የሥልጣን ጥመኞች ስለሆኑ በየስማቸው የሰየሙት ።

በፈጣሪያችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተመረጣችሁ ክቡራን አንባብያን ሆይ ይህንን ጥናት እንዳጠና ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት ከላይ በክፍል ፩ በአጭሩ እንደገለጽኩት ሁሉ የታሪክ ቁስሉ የማይረሳ ቢሆንም እንደገና ወደ ኋላ ተመልሼ አዲስ ክርክር ለማንሳት ሣይሆን ነገር ግን በተዋሕዶዎች ፤ በኦርቶዶክሶች ፤ በካቶሊኮች ፤ እንዲሁም በሌሎች የሃይማኖትና የታሪክ ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍቶች ብዙ ውሸት በጣም ጥቂት እውነት ተጽፎባቸው በማንበቤ ሲሆን አዲሱ ትውልድ እውነቱንና ሐሰቱን በታሪክ ተመራምሮ እንዲያውቅ ይሆን ዘንድ በተቻለኝ መጠን ከሐሰት በመራቅ ይህንን አጭር ጥናት ማቅረቤን በትህትና አሳስባለሁ ።



# ክፍል ፲

# ስለ ምሥጢረ ቁርባን ሥራና አፈጻጸም በ፫ቱ ታላላቅና ቀደምት ቤተ ክርስቲያኖች

## ሀ· በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ብቻ ፤

ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ ማለትም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው ። ወይም ስለ ምሥጢረ ሥላሴ (ክርስቶሎጂ) ትንተና አስቀድሜ ከላይ በ፫ቱም አብያተ ክርስቲያናት አባባል በክፍል ፪ እና ፮·፯·፰ ላይ በሚገባ የተገለጸ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስለ ምስጢረ ቁርባን አሠራርና አሰጣጥ በ፫ቱም ቤተ ክርስቲያኖች ሕግና ሥርዓት መሠረት በቅደም ተከተል አቀርባለሁ ። አመዛዝኖ ትክክለኛውን ለይቶና ተረድቶ የመምረጡን ሁኔታ ግን አስተዋይ የሆነ አእምሮ ላለው ሰው ትቸዋለሁ ።

ስለ ምስጢረ ቁርባን አሠራርና አሰጣጥ በእናት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግ መሠረት እንደሚከተለው በአጭሩ እገልጻለሁ ። ይኸውም እንደሚታወቀው ሁሉ በዚህ ጥናት ውስጥ በክፍል ፫ በተራ ቁጥር ፩ ላይ እንደ ተብራራው የእናት ኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሌሎቹ ሃይማኖቶች ከአረማዊነት ወይም ከአምልኮ ጣዖት ወደ ክርስትና እምነት የገባች ሳትሆን ነገር ግን የተሸጋገረችው በቀጥታ ከሕግ ወደ ሕግ መሆኑን በማንም ዘንድ የታወቀና የተረጋገጠ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልገውም ። እውነት ነው ይኸውም የሕገ ኦሪት የብሉይ ኪዳን ሥርዓት መሥራች እንደመሆንዋ መጠን አስቀድሜ ከላይ በክፍል ፪·፫·፬· እና ፮·፯·፰·፱ ላይ ማስረጃውን ከእነልዩነቱ ጭምር በሚገባ እንደገለጽሁት ሁሉ ዘለዓለማዊ የብርሃን አምላክ የሆነ ሕያው እግዚአብሔር በመጀመሪያ በዕለተ እሑድ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ አንድነትን የሚያመ